**የቤት ንብረትን በእጅ ማድረግ ያስመለከተ የተጣራ አቤቱታ -- ቅጽ 1D (የንግድ ንብረቶች)**
**Verified Complaint for Possession of Real Property -- Form 1D (Commercial Property)**

በእጅ ለማድረግ የሚያቀርቡት አቤቱታ የንግድ ቤት ኪራይን የሚነካ ከሆነ ቅጽ 1D መጠቀም *ይኖርብዎታል*። ንብረቱ የንግድ እስከሆነ ድረስ፣ በእጅ ለማድረግ የሚያቀርቡት የአቤቱታ ምክንያት ኪራይ አለመክፈል ወይም የማቆምያ ማስጠንቀቅያ የጊዜ ገደብ ማለፍ ምንም ቦታ ስለሌለው ይህን የአቤቱታ ቅጽ መጠቀም *ይኖርብዎታል*።

ቅጽ 1D መቼ መጠቀም እንደሚቻል የሚያሳዩ ምሳሌዎች፡

- እርስዎ የንግድ ንብረት ባለቤት ኖት፣ የንግድ ተከራይዎ ኪራይ ሳይከፍል ቀርቷል።
- እርስዎ የንግድ ንብረት ባለቤት ኖት፣ የንግድ ተከራዎ የኪራይ ውሉን ስምምነቶች ጥሷል።
- እርስዎ የግድ ንብረት ባለቤት ኖት፣ በእርስዎና በንግድ ተከራይዎ መካከል ያለው ዉል የጊዜው ገደብ ሲያልፍ።

ኖሙና፡ ቅጽ 1D እነኝህን መመሪያዎት ይከተላል። **ከዚህ ጽሁፍ ጋር በአባሪነት የተያያዘው "ናሙና ቅጽ 1D" ውስጥ በቁጥር የተጠቀሱት ሳጥኖች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎትን ያመለከታሉ።**

1. L&T የጉዳይ ቁጥር። ፀሃፊው የጉዳይ ቁጥር ስለሚሰጦት ይህንን ቦታ ክፍት ይተዉት።

2. የከሳሹን ስም፣ ሙሉ ኣድራሻና እንዲሁም ዚፕ ኮድና የስልክ ቁጥሩን በመኪና ወይም በጠራ የእጅ ጽሁፍ ይጻፉት። የፖስታ-ቤት የሳጥን ቁጥር እንደ ኣድራሻ መጻፍ የለቦትም። ጥቁር ቀለም ይጠቀሙ።

3. የተከሳሹን ስም፣ ሙሉ ኣድራሻና እንዲሁም የኣፓርትመንት ቁጥር፣ ስዊት ወይም የመሬትና ኣደባባይ ስም፣ ኲዋድራንትና (NE, NW, SE, SW) ዚፕ-ኮድ በመኪና ወይም በጠራ የእጅ ጽሁፍ ይጻፉት። ተከሳሹ በሌላ ኣድራሻ ማለት እርስዎ ለመውሰድ ከሚፈልጉት ቤት እንደሚኖር ካወቁና ኣድራሻውን ካወቁ፣ የተከሳሹን ወቅታዊ ኣድራሻ በዚህ የክስ ክፍል ውስጥ ይፃፉት። የተከሳሹን የስልክ ቁጥር ካወቁት እንዲጨምሩ ይገደዳሉ።
4. ስምዎን፣ ኣድራሻዎንና የስልክ ቁጥርዎን ጎላ ኣድርገው ይፃፉ። ከሳሽ፣ የከሳሽ ጠበቃ ወይም ክሱን የማጣራት ሥልጣን ያለው ወኪል መሆንን ለማመልከት ከሰወስቱ ሳጥኖች ኣንዱን ይምረጡ። የከሳሹ ወኪል ከሆኑ ከከሳሽሁ ጋር ያሎትን ግንኙነት ለከሳሽሁ ያስረዱ፣ ከሳሹ ድርጅት ከሆነ የሙያዎን መጠርያ ይጨምሩ።

5. ከንብረቱ ጋር ያሎትን ግንኙነትና ንብረቱን ለመውሰድ ያሎትን ሥልጣን ለማመልከት ከሰወስቱ ሳጥኖች ኣንዱን ይምረጡ። ኣከራይ ወይም የንብረቱ ባለቤት ከሆኑ መጀመርያውን ሳጥን ይምረጡ። የርስት-ንብረት ተወካይ ከሆኑና ንብረቱን ለመውሰድ የመጠየቅ ሥልጣን ካሎት የፍርድ-ቤት የውርስ ምርመራ ጉዳይ ቁጥር በተገቢው ሥፍራ ይጨምሩት። ኣከራይ፣ ባለንብረት ወይም የንብረቱ የግል ተወካይ ካልሆኑ ነገር ግን ንብረቱን የማስመለስ መብት ኣለኝ ብለው ካመኑ፣ በተሰጠው ቦታ ውስጥ የመጠየቅ ስልጣንዎን ያስረዱ።

6. በመጻፍያ መኪና ወይም በእጅ ለማስመለስ የሚፈልጉትን ንብረት ትክክለኛ ኣድራሻ በግልፅ ይጻፉት። የኣፓርትመንት ቁጥር፣ ስዊት ወይም መሬትና ኣደባባይ፣ ኲዋድራንት (NE, NW, SE, or SW) እንዲሁም ዚፕ-ኮድ።

7. በዚህ ክፍል ውስጥ ንብረቱዎን ለማስመለስ ሕጋዊ መብት እንዳሎት ለፍርድ ቤት ያስረዱ። ተከሳሹን/ተከራይን *የከሰሱበት ምክንያት* እርሱ/እርስዋ የቤት ክራይ ባለመክፈሉ/ባለመክፈልዋ ስለሆነ ይህን ሳጥን ይምረጡ። የገንዘብ ብይን ባይፈልጉም እንክዋን እንዲሁም ለተከሳሽና/ለተከራይ የቤት ክራይ ባለመክፈላቸው እንዲታረሙ/እንዲለቁ/እንዲያቆሙ ማስጠንቀቅያ የሰጡ ቢሆኑም እንክዋን ይህን ሳጥን ይምረጡ።

   a. በዚህ ክፍት ቦታ ውስጥ የተከሳሽ/የተከራይ ጠቅላላ ድምር የክራይ ዕዳ ይጻፉት። እዚህ ድምር ውስጥ የመዘግየት ቅጣት ክፍያ፡ የፍርድ ወጪዎት፡ እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎችን ኣይጨምሩ።

   b.& c. ተከሳሽ/ተከራይ ክራይ ያልከፈሉበትን የጊዜ ገደብ ይዘርዝሩ። ለምሳሌ ክራይ የሚከፈለው በመጀመርያ ወር ከሆነና ተከሳሽ/ተከራይ ፌብሩዋሪና ማርች ክራይ ካልከፈለ እርስዎ ፌብሩዋሪ 1, 2010 እስከ ማርች 31, 2010 ብለው ይጽፋሉ።.

8. በክፍል 7 ኪራይ ባለመክፈል ላይ የተመሰረተ ኣቤቱታዎን የሚመለከት ሳጥን ይምረጡና ሲጠየቁ ለምን እንደሚገባዎት በዝርዝር ያስረዱ።

9. በክፍል 7 ኪራይ ባለመክፈል ላይ የተመሰረተ ይገባኛልነትዎን የሚመለከት ሳጥን ይምረጡ። ለተከሳሽ/ለተከራይ ክራይ ባለመክፈሉ የማቆም ወይም የመታረም ወይም የመልቀቅ ማስጠንቀቅያ ከሰጡ፣ 'ሕግ እንደሚያዘው ማስጠንቀቅያ ሰጥቻለሁ' የሚለውን

ይምረጡ። የሚመለከቶትን ሳጥን ይምረጡ። ለተከሳሽና/ለተከራይ የቤት ክራይ ባለመክፈላቸው እንዲታረሙ፥ እንዲለቁ ወይም እንዲያቆሙ ማስጠንቀቅያ ከሰጡ "ሕግ የሚያዘውን ፈጽመዋል" የሚለውን ሳጥን ይምረጡ። ተከሳሽ/ተከራይ በግልጽ በክራይ-ውል ውስጥ ማስጠንቀቅያ የመቀበልን መብት ማስረከባቸው በግል ካወቁ፥ "እኔ እራሴ ውሉን አንብቤ ተከሳሽ/ተከራይ በግልጽ አስረክበዋል ..." የሚለውን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ። ይህን ሳጥን ከመረጡ፥ ተከሳሽ/ተከራይ በውሉ ዉስጥ ማስጠንቀቅያ አንፈልግም ያሉበትን አንቀጽና ቁጥር ይጨምሩ። ተከሳሽ/ተከራይ ክራይ ባለመክፈል እንዲያቆሙ ማስጠንቀቅያ የመቀበልን መብት ከውሉ በተለየ ሰነድ ከሰፈረ ሶስተኛውን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ ሆኖም ሰነዱን ከክሱ ጋር ማያያዝ ይኖርቦታል።

10. በዚህ ክፍል ውስጥ **<u>የማቆም ማስጠንቀቅያ የጊዜ ገደብ ኣልፏል</u>** ወይም ተከሳሽ/ተከራይ ንብረቱን ኣልለቀቀም በሚልና <u>በኪራይ ካለመክፈል ጋር ባልተዛመደ</u> ምክንያት ንብረቱን በእጅ ለማድረግ በሕግ እንደተደገፉ ለፍርድ ቤት ያስረዱ፣ *በእርግጥ ያቤቱታዎ መሰረት ይህ ከሆነ* ።

   a. በክፍል 10 የመረጡት ሳጥን ተከሳሽን/ተከራይን ለማስወጣት፣ የማስጠንቀቅያው የጊዜ ገደብ ኣልፏል በሚል ምክንያት ከሆነ ከዚህ በታች ከተጠቀሱትና የማስጠንቀቅያውን ይዘት የሚገልጹ ሁለት ሳጥኖች ኣንዱን መምረጥ ይኖርቦታል።

      i. ለተከሳሹ ማስጠንቀቅያ በሚሰጡበት ጊዜ በማስጠንቀቅያው ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች በሙሉ ሓቅ ከሆኑ የመጀመርያውን ሳጥን ይምረጡ።

      ii. ለተከሳሹ ማስጠንቀቅያ በሚሰጡበት ጊዜ በማስጠንቀቅያው ውስጥ የተጠቀሱት ኣንዳንድ ነጥቦች ብቻ ሓቅ ከሆኑ ሁለተኛውን ሳጥን ይምረጡና በየትኞቹ ነጥቦች እንደሚተማመኑ ያመልክቱ። ለምሳሌ ተከራይ ቤቱን ሲያበላሽና መድኅን (ኢንሹራንስ)ባለመግዛቱ የክራይ ውሉን ሲጥስ፣ ኣከራይ ለተከራይ የማረምያ ወይም የማስለቀቅያ ማስጠንቀቅያ ሲሰጥና በኋላ ግን ኣኪራይ የተሰጠው መረጃ ስህተት እንደነበረና ተከራይ ሁልጊዜ መድኅን እንደነበረው ሲገነዘብ። በእንደዚህ ሁኔታ ላይ ኣከራይ ሁለተኛውን ሳጥን በመምረጥ ተከራይ ቤቱን ኣበላሽቷል በሚለው ላይ ብቻ የይገባኛል ፍላጎቱን ያመለክታል።

   b. ማስጠንቀቅያዎን የሚመለከት ከሆነ ይህን ክፍል ይሙሉት። ማስጠንቀቅያዎ የንግድ ተከራይ የክራይን ዉል ጥሷል በሚል ላይ የተመሰረተ ከሆነ የተጣሱትን የውሉ ደንቦችን ያስረዱ። የንግድ ተከሳሽ የፈፀመውን የውል መጣስ ተግባር እንዲያርም ዕድል ተሰጥቶት ሳያርም ቢቀር፣ ተከሳሽ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ያላረማቸውን ጥሰቶችን ያስረዱ።

11. የ L&T የጉዳይ ቁጥር። ፀሃፊው የጉዳይ ቁጥር ስለሚሰጡት ይህንን ቦታ ክፍት ይተዉት።

12. ተከሳሽን/ተከራይን ለማስወጣት የሚፈልጉት **በኪራይ ኣለመክፈል ወይም የማቆምያ ማስጠንቀቅያ የጊዜ ገደብ ኣልፏል በሚል ምክንያት ሳይሆን** በሌሎች ምክንያቶች ከሆነ ይህን ክፍል ይጠቀሙ። ለእርስዎ የሚመለከቶትን ሳጥን ይምረጡ። የይገባኛል ጥያቄዎን የሚመለከት ሳጥን ከሌለ፣ "ሌሎች ምክንያቶች" የሚለውን ሳጥን መርጠው ንብረቱን በእጅ ማድረግ ይገባኛል የሚሉበትን መሰረት በዝርዝር ይግለጹ።

13. በክፍል 12 የእርስዎን ይገባኛልነትን የሚመለከተውን ሳጥን ይምረጡ። የማቆም ማስጠንቀቅያ መስጠት ግዴታ ካልሆነ፣ "ግዴታ ኣይደለም" የሚለውን ሳጥን ይምረጡ። ለተከሳሽ/ለተከራይ የማቆም ማስጠንቀቅያ ወይም የማረም ወይም የመልቀቅ ማስጠንቀቅያ ከሰጡ "ሕግ የሚያዘውን ፈጽሜኣለሁ" የሚለውን ሳጥን ይምረጡ። ተከሳሽ/ተከራይ በግልጽ በክራይ-ውል ውስጥ ማስጠንቀቅያ የመቀበልን መብት ማስወገዳቸው በግል ካወቁ፥ "እኔ እራሴ ውሉን ኣንብቤ ተከሳሽ/ተከራይ በግልጽ ኣስወግደዋል ..." የሚለውን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ። ይህን ሳጥን ከመረጡ፥ ተከሳሽ/ተከራይ በውሉ ዉስጥ ማስጠንቀቅያ ኣልፈልግም ያለበትን ኣንቀጽና ቁጥር ይጨምሩ። ተከሳሽ/ተከራይ ክራይ ባለመክፈል እንዲያቆም ማስጠንቀቅያ የመቀበልን መብቱን ማስረከቡም ከውሉ በተለየ ሰነድ ከሰፈረ ሶስተኛውን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ፣ ሆኖም ሰነዱን ከክሱ ጋር ማያያዝ <u>ይኖርቦታል</u>።

14. ይህን የኣቤቱታ ክፍል በመሙላት፣ ፍርድ ቤቱ ምን ማድረግ እንዳለበት ለፍርድ ቤቱና ለተከሳሹ እያስታወቁ ነው።

      i. የመጀመርያውን ሳጥን ከመረጡ ተከሳሽን ለማስወጣት ፍርድ ቤትን ክራይ በመክፈል ምህረት-ያለው ብይን እየጠየቁ ነው። የኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) የቤት ንብረቶችን የሚመለከቱ ኣቤቱታዎችን ብቻ ነው የሚመለከተው። ስለዚህ ተከሳሹን ለማስወጣት ፍላጎት ከሌሎት፣ ጉዳይዎን በፍርድ ቤት ቅርንጫፎች ማለትም የትናንሽ ኣቤቱታዎችና ማስታረቅያ ወይን በሲቪል ጉዳዮች ቅርንጫፍ ያቅርቡ። የኣቤቱታዎ ምክንያት ክራይ ኣለመክፈል ብቻ ከሆነ ይህን ሳጥን መምረጥ *ይኖርብዎታል*።

      ii. ሁለተኛውን ሳጥን ከመረጡ ተከሳሽን ለማስወጣት ፍርድ ቤትን ምህረት-የሌለው ብይን እየጠየቁ ነው።የኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) የቤት ንብረቶችን የሚመለከቱ ኣቤቱታዎችን ብቻ ነው የሚመለከተው። ስለዚህ ተከሳሹን ለማስወጣት ፍላጎት ከሌሎት፣ ጉዳይዎን በፍርድ ቤት ቅርንጫፎች ማለትም

የትናንሽ አቤቱታዎችና ማስታረቅያ ወይን በሲቪል ጉዳዮች ቅርንጫፍ ያቅርቡ። የአቤቱታዎ ምክንያት ክራይ ባለመክፈልና በተጨማሪም በሌሎች ምክንያቶች ከሆነ ይህን ሳጥን መምረጥ ይችላሉ።

iii. ፍርድ ቤት ተከሳሹ ለእርስዎ ባልከፈለው የኪራይ ዕዳ የገንዘብ ብይን እንዲያደርግ ከፈለጉ ሁለተኛውን ሳጥን ይምረጡ። መፈረድ ያለበትን የገንዘብ መጠን በቀኝ በኩል ባለው ክፍት ቦታ ይግለጹ። የገንዘብ ብይን ኪራዩን ከተከሳሹ ለመጠየቅ ይረዳዎታል፥ ለምሳሌ ተከሳሹ በፈቃዱ ካልከፈለ ደሞዙን ማስያዝ ይቻላል።

iv. ፍርድ ቤት ተከሳሹን በየወሩ የቤት ኪራይ ለፍርድ ቤት እንዲያስከፍለው ከፈለጉ ሶስተኛውን ሳጥን ይምረጡ። ጉዳይዎ በመጀመርያ የፍርድ ቀን ካልተፈጸመ ጉዳይዎ እስኪዘጋ ድረስ ገንዘቡ በልዩ አካውንት ይቀመጣል። (ፍርድ ቤት ማዘዝ የሚችለው የመጪውን ክራይ ማለት ከመጀመርያ የፍርድ ቀን ጀምሮ ጉዳዩ እስከሚፈጸም ድረስ ያለውን ጊዜ እንጂ ያለፈውን ክራይ ኣይደለም)።

15. እርስዎ ክሱን ከፈረሙ በኋላ የሰነድ-ኣጽዳቂው (Notary Public) ወይም የፍርድ ቤት ጸሓፊው ይህን ክፍል ይፈጽመዋል። ክሱ በኣከራይና ተከራይ ፀሓፊ ቢሮ (Landlord and Tenant Clerk's Office)በነጻ ሊጸድቅ ይችላል።

16. በክፍል 4 የተጠቀሰው ሰው ክሱን በኣከራይና ተከራይ ጸሓፊ ቢሮ (Landlord and Tenant Clerk's Office) በሚሰራ የሰነድ-ኣጽዳቂ ወይም ጸሓፊ ፊት በመቅረብ በዚህ ቦታ መፈረም ኣለበት።

17. በክፍል 4 እንዲሁም በክፍል 16 በፊርማ መስመር ላይ ስሙ የተጠቀሰው ሰው የሚፈርመው ድርጅትን በመወከል ከሆነ፥ ይህ ሰው ማዕርጉን/ማዕርጉዋን በተሰጠው መስመር ላይ መጨመር ኣለበት/ኣለባት(ለምሳሌ ፕረዚደንት፣ ገንዘብ-ያዥ፣ የንብረት ኣስተዳዳሪ)።

18. ይህ ኣስፈላጊ ነጥብ እርስዎን ሊመለከት ይችላል። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (District of Columbia) ባለስመ-ጥሩ ጠበቃ ካልሆኑ፣ ጉዳዩ ኣንዲቀጥል ከመጠየቅ በስተቀር ሌላ ሰውን በመወከል በኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) በመቅረብ ጉዳዮችን ለመፈጸም ከሞከሩ ያለፍቃድ የሕግ ሥራ እንደሰሩ ሊቆጠር ይችላል።

19. በጠበቃ የሚወከሉ ከሆኑ፣ እሱ/እስዋ የጥብቅና ቁጥርና የኢሜል ኣድራሻ በመጨመር ይህን ክፍል መሙላት ኣለበት/ኣለባት። በጠበቃ የማይወከሉ ከሆኑ ይህን ክፍል በራስዎ መረጃ ይምሉት። ጠበቃ ካልሆኑ የጠበቃ ሞያ ቁጥርና ኢሜይል (Unified Bar No. and Email Address) የሚለውን ቦታ ክፍት ይተዉት። የክሱን ማጣራት የሚለውን ክፍል ከከሳሽ የተለየ ሰው ከሞላው፣ ከሳሽ ወይም የከሳሽ ጠበቃ ክሱን በዚህ ክፍል ዉስጥ መፈረም ኣለባቸው።

20. ይህን ክፍል ክፍት ይተውት። ክሱን ሲያቀርቡ ፀሓፊው የሚፈቀደውን ጠቅላላ ወጪ እዚያ ውስጥ ይጽፈዋል።

# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሲቪል ክፍል
## የኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ
510 4th STREET, N.W., Building B, Room #110, Washington, D.C. 20001 Telephone (202) 879-4879

የጉዳይ ቁጥር LTB______1__________

______________2________________________ከ
ከሳሽ (ሾች)

________________________3________________________________ጋር
ተከሳሽ (ሾች)

________________________________________________________________

________________________________________________________________
ኣድራሻ (ፖስታ ሳጥን ያልሆነ

ኣድራሻ

______________________________________
ከተማ ስቴት ዚፕ ኮድ

ዋሽንግተን ዲሲ______________________________________________________
ዚፕ ኮድ

__________________________________________
ስልክ ቁጥር

__________________________________________________________________________
ስልክ ቁጥር (*ከታወቀ*)

## የቤት ንብረትን በእጅ ማድረግ የሚመለከት የተረጋገጠ ኣቤቱታ -- ቅጽ (ፎርም) 1D
(የንግድ ንብረት)

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ss:

1. እኔ *(ስም፣ኣድራሻ፣ እንዲሁም ስልክ ቁጥር)* ________________4________________ እዚህ ኣቤቱታ ውስጥ ስለቀረቡት ነጥቦች ግንዛቤ እንዳለኝና ከሳሽ ወይም የከሳሽ ጠበቃ ወይም የከሳሽ ወኪል በመሆን ይህን ኣቤቱታ ለማጣራት ስልጣን እንዳለኝ እምላለሁ ወይም ኣረጋግጣለሁ። እውነት ሆኖ ካልተገኘ በውሸት ምስክርነት እከሰሳለሁ። ከከካሹ ጋር ያለኝ ግንኙነት *(ያስረዱ፣ ከሳሽ ኮርፖረሽን ከሆነ ሹመትዎን ይጨምሩ*___________________________________________________________________

2. 5ከሳሽ፡ ኣከራይ ወይም ባለቤት ነው፣ ወይም የርስትና ንብረት የግል ተወካይ ሆኖ ብጉዳይ ቁጥር_____መሰረት ተሹሙዋል ንብረቱንም በእጅ የማድረግ ስልጣን ኣለው፥ ወይም ኣከራይ፣ ባለቤት ወይም የግል ወኪል ኣይደለም፥ ነገር ግን በእጅ ለማድረግ የመጠየቅ መብት ኣለው ምክንያቱም (*ያስረዱ*)_______________________________________________________

3. ከሳሽ በ__________________6__________________________________ዋሽንግተን ድሲ የሚገኘውን የንግድ ንብረቱን በእጅ ማድረግ ይፈልጋል። ንብረቱ በተከሳሽ ማለት ሙብት በሌለው ተከራይ እጅ ይገኛል። ከሳሽ በእጅ ማድረግ የሚፈልግበት ምክንያት፡

   A. ተከሳሽ $__a_____ ድምር የቤት ክራይ ከ_____b_____እስከ___c____ ለኣከራይ ባለመክፈሉ ነው።
   ተከሳሽ የሚከተሉት ዕዳዎች ኣሉበት፡

   8 መደበኛ የወር ክራይ $______________
   የጋራ ቦታዎችን መጠበቅያ $ _____________(*ያስረዱ*)__________________________________________________________________________።
   የመሰረታዊ ኣገልግሎትወጪዎች $_________(*ያስረዱ*)__________________________________________________________________________።
   የቀረጥ ወጪዎች $___________*ያስረዱ*____________________________________________________________________________________።
   የመዘግየት መቀጮ በየወሩ $__________ከ__________________እስከ______________________ወራት።
   ተገቢ የጠበቃ ክፍያ $___________እስከ ዛሬ ድረስ፣ በክራይ ዉል ኣንቀጽ ___________________መሰረት።
   ሌላ ሂሳብ $ _______________ለ (*ያስረዱ*)___________________________________________________።

   ሕግ እንደሚያዘው የማስለቀቅያ ማስጠንቀቅያ ተልኮ ነበር፣ ወይም እኔ ዉሉን በደንብ ኣንብቤው ተከሳሽ በግልፅ በኣንቀጽ_____ቁጥር_____የማስቆምያ ማሳሰብያ የመቀበሉን መብት ኣስረክብዋል፥ ወይም ተከሳሽ በግልፅ በሌሎች ሰነዶች ያንን መብት ኣስረክብዋል(*ሰነድ ያያይዙ*)።

   B. ተከሳሽ ባገባብ የተሰጠውን የማቆም ወይም የመሰረዝ ማስጠንቀቅያ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ንብረቱን ሳይለቅ ቀርቷል *(የማስጠንቀቅያና ማስጠንቀቅያ የመሰጠቱን ማረጋገጫ ቅጅ ያያይዙ*)።

   1) የማስጠንቀቅያው ይዘት፡
      ማስጠንቀቅያው ውስጥ የተጠቀሱት ነጥቦች ማስጠንቀቅያው በሚሰጥበት ጊዜ ሓቅ ነበሩ፥ ወይም
      ከሳሽ በሚቀጥሉት ነጥቦች ማለት ከተያያዘው ማስጠንቀቅያ ውስጥ የሚገኙና በዛን ጊዜ ሓቅ ነበሩ፡
      (*ዘርዝር*)____________________________________________________________________________________________________________።

   2) ማስጠንቀቅያውን ማክበር፡ *(የሚመለከትዎ ከሆነ ይሙሉት)*

      a. በማስጠንቀቅያው ውስጥ የተገለጸው የተከሳሽ ተግባር የሚከተሉትን የክራይ ዉል ኣንቀጽ ቁጥርን ጥሳል፣_____________________________________________________።

      b. በማስጠንቀቅያው ዉስጥ ከተጠቀሱት ጥሰቶች ፣ ተከሳሽ የሚከተሉትን ጥሰቶች በማስጠንቀቅያ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ሳያርም/ሳያስወገድ ቀርቷል፡_________________________
      ______________________________________________________________________________________________________________________።



ሁለቱን ገጾች ይሙሉ

የጉዳይ ቁጥር
LTB_______________________11___________________

C. 12 በሚከተሉት ምክንያቶች፡
ተከሳሽ የክራይ ዉሉ ከተቃጠለ በኋላ ቤቱን ይዞታል።
ተከሳሽ ተከራይ ኣይደለም፣ ስለዚህም ቤቱን የመያዝ ሕጋዊ መብት የለውም።
ሌላ ምክንያት *(በዝርዝር ያስረዱ)*_______________________________________________

_______________________________________________

13የማቆም ማስጠንቀቅያ መስጠት፡ ግዴታ ኣይደለም ወይም ሕግ እንደሚለው ተሰጥቶ ነበር፣ ወይም እኔ ዉሉን በደንብ ኣንብቤው ተከሳሽ በግልፅ በኣንቀጽ_____ቁጥር____የማስቆምያ ማሳሰብያ የመቀበሉን መብት ኣስረክብዋል፥ ወይም ተከሳሽ በግልፅ በሌሎች ሰነዶች ያንን መብት ኣስረክብዋል(*ሰነድ ያያይዙ*)።

ስለዚህ ከሳሽ ፍርድ ቤትን የሚጠይቁት *(የሚመለከቱትን በሙሉ ይምረጡ)*

14 የተባለውን ንብረት በእጅ ለማድረግ ምህረት ያለው ብይን (ኪራይ በመክፈል ተከራይነት ማስመለስ)ና ፀሓፊው ወጪዎችን እንዲቀርጥ።
የተባለውን ንብረት በእጅ ለማድረግ ምህረት የሌለው ብይን (ተከራይነት የማስመለስ መብት የሌለበት)ና ፀሓፊው እንዲቀርጥ።
የኪራይ፣ ኣንደ ኪራይ የሚቆጠሩ ክፍያዎችና የመዘግየት ክፍያዎችን የሚያጠቃልል የገንዘድ ብይን $_____________________።
ጉዳዩ እስከሚፈረድ ድረስ የወደፊት ኪራይ በሙሉ ለፍርድ ቤት የምዝገባ ክፍል እንዲከፈል የሚያዝ የመከላከያ ፍርድ።

በፍቃዱ ከእኔ ፊት ቀርቦ በዚህ_____ዕለት ________ 20________ 16_______________________________________

15

ከሳሽ/የከሳሽ ጠበቃ/የከሳሽ ወኪል ዕለት

____________________ ___________________________ 17_______________________________________

የሰነድ ኣጽዳቂ ስልጣኔ የሚቃጠልበት ጊዜ የፈራሚ ሰም ሹመት (*ካለ*)

18 **ኣስፈላጊ ማሳሰብያ ለተሳታፊዎች፡** የይግባኝ ፍርድ ቤት ደንብ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሲቪል ደንብ 101 እንዲሁም የኣከራይና ተከራይ ደንብ ቁጥር 9 ያለፍቃድ የጥብቅና ስራ መስራትን ይከለክላል። ማንኛውም ሰው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ስሙ-ጥሩ ጠበቃ ያልሆነ፣ እርሱ ወይም እርስዋ ሌላ ሰው በመወከል በኣከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (Landlord and Tenant Branch) በመሄድ ጉዳዩ እንዲቀጥል ለመጠየቅ ብቻ ካልሆነ፣ ያለፍቃድ የጥብቅና ስራ ዉስጥ እንደተሰማራ መገንዘብ ኣለበት።

19_____________________________________________ _________________________________________

ከሳሽ/የከሳሽ ጠበቃ የሕግ ሙያ ቁጥር የፍርድ ቤት ፀሓፊ

_____________________________________________

ኣድራሻ ዚፕ ኮድ

_____________________________________________ የዚህ ክስ ወጪዎች እስከዛሬ ድረስ $_______20______ ናቸው።

የስልክ ቁጥር የኢሜይል ኣድራሻ (ለጠበቃ ብቻ)

የኣማርኛ ትርጉም ለማግኘት (202) 879-4828 ይደውሉ



ሁለቱን ገጾች ይሙሉ

Translated by JTG, inc. 02/2017